## ምዕራፍ ፯

### በቃና ዘገሊላ ምንባብ

፩ በስመ እግዚአብሔር ሥሉስ ኅቡረ
ህልዎ ልዑል ዘኢይረክብዎ ክቡት ዘኢይሬእ
ይዎ:እሳት ዘኢይለክፍዎ:መንፈስ ዘኢይገስስዎ:
ኃይል ዘኢይሌብውዎ:ንጉሥ ዘኢይሠይምዎ
አምላክነ በመለኮቱ ወአቡነ በኂሩቱ: ሎቱ ሰብ
ሐት ለዓለመ ዓለም አሜን::

፪ ንጽሕፍኬ ዘለፋሆሙ ለረሲዓን እለ
ይብሉ ተመይጠ ቃለ መለኮት ለከዊነ ሥጋ
ወደም ወለከዊነ ዓጽም ወጸጉር ወአሥራው::
ይመስለክሙኑ ኦ አብዳን ከመ ተመይጠ ኃይለ
መለኮት ለከዊነ ሥጋ ወትስብእትኒ ለከዊነ መለ
ኮት:አኮ ከመ ብእሲተ ሎጥ ዘኮነት ሐውልተ
ፄው: ወአኮ ከመ ናቡከደናጾር ንጉሠ ከላውዴ
ዎን ዘኮነ አርዌ ገዳም ወካዕበ ተመይጠ ለከዊነ
ሰብእ:: ወአኮ ከመ ማየ ቃና ዘኮነ ወይነ እሉ
ሠለስቱ ተመይጡ እምህላዌሆሙ አኮ በፈቃደ
ሙ አላ በፈቃደ እግዚአብሔር::ብእሲተ ሎጥኒ
ኮነት ሐውልተ ፄው በእንተ ዘዐለወት ትእዛዘ
እግዚአብሔር ዘአዘዛ ከመ ኢትትመየጥ መንገለ
ሰዶም ወገሞራ::ወሶበ ተመይጠት ለነጽሮ ርእ
የት ጢሰ ከመ ጢሰ እቶን::ወእምዝ ኮነት ፍጹ
መ ሐውልተ ፄው ኢተኀድገ ላቲ እስተንፋስ ለአ
ፄንዎ ወኢመንፈስ ለአንሳሕስሖ እስመ እግዚአ
ብሔር አእበና ወሜጠ ህላዌሃ ለከዊነ ሐውልት::
ዘፍ፲፱፥፲፭-፳፮

፫ ወናቡከደነጾርኒ ንጉሥ ኮነ
አርዌ ምድር እስመ አዕበየ ኀሊናሁ እንዘ ይኄሊ
ከመ እግዚአ ዓለም ውእቱ በሥልጣነ ርእሱ::
ወኢገነየ ለስብሐተ እግዚአብሔር ዘወሀቦ መዊአ
ወሥልጣነ ዲበ ኵሉ አጽናፈ ዓለም::ወእምዝ
ረሰዮ እግዚአብሔር አርዌ ገዳም::ገሠጸ በተአር
ውዮ ወአንበሮ በአንስሶ::ኢኀደገ ሎቱ ጸጉረ ወኢ
አጽፋረ ዘእጓለ እመሕያው አላ ገብረ ሎቱ አጽ
ፋረ ዘእንስሳ ወጸጉረ ዘአራዊት:: ወነበረ ውስተ
ገዳም ፯ ዓመተ እንዘ ይትረዐይ ሣዕረ ምስለ
ሐለስትዮታት እስመ እግዚአብሔር መስተበቅል
ለዕቡያን::ወካዕበመ ሜጠ እግዚአብሔር ኀሊናሁ
ወናቡከደነጾርኒ ንጉሥ ኮነ አርዌ ኀበ ልቡና ሰብ
እ ወራእዮኒ ከመ ኀበ መልክዐ እጓለ እመሕያው
አንበሮ ዲበ መንግሥቱ:እስመ እግዚአብሔር
መስተሣህል ለነሳሒያን::ወእምዝ ገነየ ውእቱኒ
ለስብሐተ ልዑል ወአእመረ ከመ እግዚአ መንግ
ሥት ወነገሥት እግዚአብሔር:: ዳን፬፥፳፰-፴፯

## ምዕራፍ ሰባት

### በቃና ዘገሊላ ምንባብ

፩ በህልውና አንድ በሚሆን ሦስት
የማያገኙት ከፍ ያለ የማያዩት የተሠወረ የማ
ይይዙት እሳት የማይዳስሱት መንፈስ በማስተ
ዋል የማይወስኑት ኃይል የማይሾሙት ንጉሥ
በሆነ በእግዚአብሔር ስም በመለኮቱ አምላካችን
በቸርነቱም አባታችን ነው ለርሱ ምስጋና ይገባል
ለዘላለሙ አሜን::

፪ የመለኮት ቃል ሥጋና ደም አጥንትና
ፀጉር ሥሮችንም ወደመሆን ተለወጠ የሚሉ
ዝንጉዎችን ተግሣጽ እንጽፋለን:: እናንተ ሰነፎች
የመለኮት ኃይል ሥጋን ወደመሆን ሰብእናም
መለኮትን ወደ መሆን የተለወጠ ይመስላችኋልን
የጨው ሐውልት እንደ ሆነች እንደ ሎጥ ሚስ
ት አይደለም የበረሀ አውሬ እንደሆነ ዳግመኛም
ሰው ወደመሆን እንደተለወጠ እንደ ከላውዴዎስ
ንጉሥ እንደ ናቡከደነፆር አይደለም:: ወይን እን
ደሆነ እንደ ቃናም ውኃ አይደለም:: እኒህ ሦስቱ
ከባሕርያቸው ተለወጡ በፈቃዳቸው አይደለም
በእግዚአብሔር ፈቃድ እንጂ::የሎጥ ሚስት ወደ
ሰዶምና ገሞራ እንዳትመለስ ያዘዛትን የእግዚአ
ብሔርን ትእዛዝ ስለተላለፈች የጨው ሐውልት
ሆነች ለመመልከት መለስ ባለች ጊዜ ጢሱን እን
ደ እቶን ጢስ አየች ከዚያም ፍጹም የጨው
ሐወልት ሆነች ለማሽተትም ትንፋሽ ለመንቀሳ
ቀስም መንፈስ አልቀረላትም እግዚአብሔር ደን
ጊያ አድርጓታልና ባሕርይዋንም ሐውልት ወደ
መሆን ለውጧልና:: ዘፍ፲፱፥፲፭-፳፮

፫ ንጉሥ ናቡከደነጾርም በገዛ ሥል
ጣኑ የዓለም ጌታ እንደሆነ አስቦ ኅሊናውን አስ
ታብዮአልና አውሬ ሆነ::በዓለም ዳርቻዎች ሁሉ
ላይ ማቸነፍንና ሥልጣንን ለሰጠው ለእግዚአ
ብሔር ክብር አልተገዛምና:: ከዚህ በኋላ እግዚአ
ብሔር የበረሀ አውሬ አደረገው አውሬ በመሆን
ገሠፀው እንስሳም በመሆን አኖረው ጸጉርና የሰ
ው ጥፍሮችን አልተወለትም የእንስሳ ጥፍሮ
ችንና የአራዊትን ጠጉር አደረገለት እንጂ በበረ
ሀም ሰባት ዓመት ያህል ከእርያዎች ጋር ሣር
እየተመገበ ኖረ እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን
የሚ በቀል ነውና:: ሁለተኛም ኀሊናውን ወደ
ሰው ልብነት መልኩንም ወደ ሰው ልጅ መልክ
መለሰ በመንግሥቱም አስቀመጠው እግዚአ
ብሔር ንስሓ ለሚገቡ ይቅርባይ ነውና::ከዚህም
በኋላ እር ሱም ለልዑል ክብር ተገዛ
እግዚአብሔር የመንግ ሥትና የነገሥታት ጌታ
እንደሆነ ዐወቀ:: ዳን፬፥፳፰-፴፯

፬ ወማየ ቃናኒ ዘኮነ ወይነ አኮ ወይን ዘል
ማድ ዘገብርዎ በምክያድ ዐጸርዎ በውስተ
ማኅበብ አላ ወይነ መንክራቲሁ ለወልደ እግዚአ
ብሔር በዘኢይትኀፈር መርዓዊ ወበዘይረውዩ
ሰብአ ከብካብ ፡እስመ ትቤሎ እሙ ለእግዚእ
ኢየሱስ ወይንኬ አልቦሙ እስመ ኀለቀ ወይ
ኖሙ አቅልልኬ ዘንተ፡፡ወይቤላ እግዚእ ኢየሱስ
ምንተ ትብልኒ ብእሲቶ እስመ ዓዲ ኢበጽሐ
ጊዜየ፡፡ ወአውሥኣ ዘከመ ይኄይስ ለዘዝጉብ
ፍቅረ ዚአሃ ውስተ ልቡ፡፡ይእቲሰ አስተብቍዐቶ
በእንተ ወይን ምድራዊ ውእቱኒ አውሥአ በአመ
ሥጥሮ በእንተ ወይነ ደሙ ዘይትቀዳሕ እም
ገቦሁ፡፡ ወዘይቤሰ ኢበጽሐ ጊዜሁ ይትፌከር ኀበ
ብሂለ ኢበጽሐ ሰዓተ ተረግዞትየ ከመ አርው
ዮሙ ለመሀይምናን በወይነ ምሥጢር ዘእምገቦየ
ውኅዘ እስመ ተረፋኒ ሠላስ ዓመታትየ በዘአርኢ
መንክራተ አቡየ በዲበ ምድር ወበዘእትዌከፍ
ረሀበ ወጽምአ ወኵሎ ዓጸባ በሥጋ ዘነሣእኩ
እምኔኪ በዘእሬ ፍቅ ምስለ ኃጥአን ወበዘእትገሰስ
እምዘማት፡፡ ዮሐ፪፥፩-፲፩

፭ ወእምቦ ዘይቤ በእንተ ወይነ ተአምሪሁ
ይቤ ዘንተ፡፡ አነኒ እብሎ በጽሐኬ ጊዜሁ
ኢያጉንደየ ገቢሮቶ ሶቤሃ አዘዘ ይቅድሕዎ
ለማይ ወይደዩ ውስተ መስብክተ እብን ስሱ፡፡
ተመይጠ ህላዌሁ ለከዊነ ወይን፡፡ አኮ መስብክት
ዘሜጣሁ ለማይ ኀበ ከዊነ ወይን አላ ሜጠ
ለማይ ኀበ ከዊነ ወይን ዘአዘዘ ከመ ይቅድሕዎ
ኀበ መስብከት፡፡ እመሰ መስብክት ይመይጣሁ
ለማይ ኀበ ከዊነ ወይን አኮኑ እማንቱ ዘዘልፈ
ያጥሀሩ አይሁድ ውስቴቶን ዘያገምራ በበክልዔ
ወበበ ሠላስ መሣፍር ዘቀሱት፡፡ወይነ ቃናሰ
ተመሰለት በሕገ ኦሪት እስመ ኢያጽደቀቶሙ
ለእለ ሰትይዋ ወባሕቱ አስተፍሥሐት አልባቢ
ሆሙ በጣዕመ መዓዛሃ፡ወከማሁ ኦሪትኒ ኢያ
ጽደቀቶሙ ለእለ ተወከፍዋ ቀዲሙ ወባሕቱ
አስተፍሥሐት አልባቢሆሙ በአጽምኦታ እስመ
ቃለ እግዚአብሔር ይእቲ፡ወበእንተዝ ይቤ ጳው
ሎስ ወሶበ ስእኑ ጸዲቀ በሕገ ኦሪት ፈነወ እግዚ
አብሔር ወልዶ ወተወልደ እምብእሲት ወገብረ
በሕገ ኦሪት ከመ ይሣየጦሙ ለእለ ውስተ
ኦሪት፡፡ ገላ፬፥፬ ዕብ ፬፥፱

፮ ወከመ ተመይጠ ማይ በቃና ለከዊነ
ወይን ወከማሁ ተመይጠ በትረ ሙሴ በደብረ
ሲና ለከዊነ አርዌ ምድር ዘይትሐወስ እስከ ጕየ
ነቢይ እምቅድመ ገጹ፡ወካዕበ ተመይጠ ኀበ ከዊነ
በትር እስከ ደነነ ነቢይ ወነሥኦ ወገብረ ተአምረ
በውእቱ በትር በቅድመ ፈርዖን ወበቅድመ ዐበይ
ቱ፡፡ወወይነ ደሙ ለእግዚእ ኢየሱስ ተመሰለ
በሕገ ወንጌል እስመ ክህለ አርውዮ ወክህለ አጽ
ድቆ፡፡እስመ ይቤ መድኃኒነ እስመ ሥጋየኒ መብ
ልዐ ጽድቅ ዘበአማን ወደምየኒ ስቴ ሕይወት ዘበ
አማን፡ ዘበልዐ ሥጋየ የሐዩ በእንቲአየ ወዘሰትየ

፬ ወይን የሆነ የቃና ውኃም በመጭ መቂያ
ጨምቀው በመጥመቂያ ውስጥ የጠ መቁት
የልማድ ወይን አይደለም፡ ሙሽራ እንዳ ያፍር
ሠርገኞችም እንዲረኩ የተሰጠ የእግዚ አብሔር
ልጅ የተአምራቱ ወይን ነው እንጂ ፡፡ የጌታ
ኢየሱስ እናቱ ወይን እኮ የላቸውም ወይ ናቸው
አልቋልና እባክህ ይህን ችግር አስወግድ
ብላዋለችና፡፡ ጌታ ኢየሱስም አንቺ ሴት ከአንቺ
ምን አለኝ ገና ጊዜዬ አል ደረሰምና አላት፡በልቡ
ለተከማቸ ፍቅሯ በሚሻል ነገር መለሰላት እርሷ
ስለምድራዊ ወይን ለመነችው እርሱም ከጐኑ
የደሙ ወይን በምሥጢር መለሰ፡፡ ጊዜዬ አልደረ
ሰም ያለው የአባቴን ድንቆች በምድር ላይ በምገ
ልጥበት ገንዘብ ካንቺም በነሣሁት ሥጋ ረሀብንና
ጥምን ጭንቁንም ሁሉ በምቀበልበት ገንዘብ
ከኃጥአን ጋር በምቀመጥበት በአመንዝሮችም
በምደሳሰበት ገንዘብ ሦስት ዓመታት ቀርተውኛልና
ከጐኔ በፈሰሰ የምሥጢር ወይን ምእ መናንን
አረካቸው ዘንድ የምወጋበት ሰዓት አል ደረሰም
ተብሎ ይተረጐማል፡፡ ዮሐ፪፥፩-፲፩

፭ ይህን ስለ ተአምራቱ ወይን ተናግሮ
ታል የሚል ቢኖር እኔም ጊዜው እኮ ደረሰ ማድ
ረጉንም አላዘገየም እለዋለሁ፡ያንጊዜም ውኃውን
ቀድተው በስድስቱ የደንጊያ ጋኖች እንዲጨምሩ
አዘዘ ባሕርዩም ወይን ወደመሆን ተለወጠ፡፡
ጋኖች ውኃውን ወይን ወደመሆን የለወጡት
አይደለም እርሱ ወደ ጋኖች እንዲቀዱት ያዘዘውን
ውኃ ወይን ወደ መሆን ለወጠው እንጂ ጋኖች
ውኃውን ወይን ወደመሆን የሚለውጡትስ ቢሆ
ን አይሁድ ዘወትር ሁለት ሁለት ሦስት ሦስት
ማድጋ በሚይዙ በእነዚያ ጋኖች ውስጥ የሚያ
ጠሩባቸው አይደሉምን፡፡የቃና ወይን በኦሪት
ሕግ ተመሰለች የጠጡአትን አላጸደቀቻቸውምና
ነገር ግን በመዓዛዋ ጣፋጭነት ልባቸውን ደስ
አሰኘች እንዲሁ ኦሪትም ቀድመው የተቀበሉአ
ትን አላ ጸደቀቻቸውም ነገር ግን የእግዚአብሔር
ቃል ናትና እርሷን በመስማት ልባቸውን ደስ
አሰኘች ስለዚህም ነገር ጳውሎስ በኦሪት ሕግ
መጽደቅ በተሳናቸው ጊዜ እግዚአብሔር ልጁን
ላከ ከሴትም ተወለደ በኦሪት ያሉትንም ይዋጅ
ዘንድ የኦሪትን ሕግ ፈጸመ አለ፡፡ ገላ፬፥፬ ዕብ
፬፥፱

፮ ውኃው በቃና ወይን ወደ መሆን
እንደ ተለወጠ እንዲሁ የሙሴ በትር በደብረ
ሲና ነቢዩ ከፊቱ እስኪሸሽ ድረስ የሚንቀሳቀስ
እባብ ወደመሆን ተለወጠ፡፡ ሁለተኛም ነቢዩ ጐን
በስ ብሎ እስኪያነሣው ድረስ በትር ወደ መሆን
ተመለሰ በዚያም በትር በፈርዖንና በታላላቆቹ
ፊት ተአምራትን አደረገ የጌታ ኢየሱስም የደሙ
ወይን በወንጌል ሕግ ተመሰለ ማርካትና ማጽ
ደቅን ችሏልና መድኃኒታችን ሥጋዬ እውነተኛ
የጽድቅ ምግብ ነው ደሜም እውነተኛ የሕይወት
ውኃ ነው ሥጋዬን የበላ የእኔን ሥጋ ስለበላ
በሕይወት ይኖራል ደሜንም የጠጣ ሞትን

ደምየ አይጥዕሞ ለሞት።ወበእንተወንጌሉሂ ይቤ ኵሉ ዘአምነ ወተጠምቀ ይድኅን ወዘሰ ኢአምነ ይዴየን። ዘጸ፬+፪ ማር፲፮+፲፮ ፮+፶፮

፺ ንትመየጥኬ ኀበ ዜና ማኅሠሠ ወይን ዘእምአምላክ እምኀበ ወልዳ።በእንተ ምን ትኬ አስተበቍዐቶ እንዘ ትብል ወይንኬ አልቦ ሙ እስመ ኅልቀ ወይኖሙ።አእመረትኑ ከመ ይቀድሕ ወይነ እማይ እስመ ኢገብረ ከመዝ እምቅድመ አሜሃ።በከመ ይቤ ዮሐንስ ወንጌላዊ ወዝንቱ ውእቱ ቀዳሚ ተአምር ዘገብረ እግዚእ ኢየሱስ በቃና ዘገሊላ አርአዮሙ ስብሐቲሁ ወአምኑ ቦቱ አርዳኢሁ። ዮሐ ፪+፲፩

፰ ኢያእመረትኬ ድንግል ከመ ይመይጦ ለማይ ኀበ ከዊነ ወይን።ወባሕቱ አእመረት ከመ በጽላሎተ አብ ፀንሰቶ ወበኃይለ ልዑል ወለደቶ። ወበእንተዝ ተሐበለት ድንግል ከመ ታስተብቍዖ በእንተ ወይን እስመ ተጠየቀት አቡሁ ሰማያዌ እምኀበ መልአክ ዘአብሰራ።ወበእንዝ ትቤ በልባ እስመ ወልዱ ለገባሬ መንክራት ይገብር መንክረ ከመ አቡሁ። ወአርዳኢሁሰ ኢያስ ተብቍዕዎ በእንተ ወይን እስመ ኢያእመሩ አቡሁ ወይመስሎሙ ወልደ ዮሴፍ ውእቱ እስመ ኢነገሮሙ መልአክ በከመ ነገራ ለእሙ። ወእም ድኅረ ገብረሂ መንክራተ ኢአምንዎ ከመ ወልደ እግዚአብሔር ውእቱ ዘእንበለ ከመ አሐዱ እምነቢያት።

፴ ወበእንተዝ ይቤሎሙ በደወለ ቂሳርያ ዘፊልጶስ መነሂ ይብልዎ ሰብእ ለወልደ እጓለ እመሕያው፡ ወይቤልዎ አርዳኢሁ ቦ እለ ይብሉከ ኤልያስሃ ወቦ እለ ይብሉከ ኤርምያስሃ ወቦ እለ ይብሉከ ፩ እምነቢያት ቀደምት ተንሥአ። ወይቤሎሙ አንትሙኬ መነ ትብሉኒ ከዊነ።ወአውሥአ ስምዖን ጴጥሮስ ወይቤሎ አንተ ውእቱ ክርስቶስ መሲሕ ወልዱ ለእግዚአብሔር ሕያው። ወእንዘ ይትናበብ ምስለ ወልድ በደወለ ቂሳርያ ዘፊልጶስ ግብተ ተመሥጠ ኅሊናሁ ለጴጥሮስ በአክናፈ መንፈስቅዱስ ወበጽሐ ኀበ ህሉና አብ። ወበህየኒ ረከቦ ለእግዚእ ኢየሱስ እንዘ ይነብር በየማነ አብ። ወበእንተዝ ይቤሎ ለወልድ አንተ ውእቱ ክርስቶስ ወልዱ ለእግዚአብሔር ሕያው። ወውእቱኒ ስምዐ ኮነ ሎቱ ከመ ኢተከሥተ ሎቱ በሕሊና ሥጋ። ወይቤሎ እስመ ኢከሠተ ለከ ዘሥጋ ወደም አላ አቡየ ዘበሰማያት። ጴጥሮስ ተመርሐ እምኀበ መንፈስቅዱስ ወነሥአ ልቡና እምኀበ አብ ወተሠይመ ኤጲስ ቆጶሰ እምኀበ ወልድእስመ ይቤሎ አንተ ኰኵሕ ወላዕሌከ አሐንፃ ለቤተክርስቲያንየ ወለከ እሁበከ መራኁተ ዘመንግሥተሰማያት።ዘአሰርከ በምድር ይኩን እሡረ በሰማያት።ወዘፈታሕከ በምድር ይኩን ፍቱሐ በሰማያት። ማቴ፲፮+፲፫-፳

አይቀምሰውም ብሏል እኮን።ስለወንጌሉም ያመነ የተጠመቀ ሁሉ ይድናል ያለመነ ግን ይፈረድበታል አለ። ዘጸ፬+፪ ማር፲፮+፲፮ ፮+፶፮

፺ የአምላክን እናት ከልጇ ዘንድ ወይንን ወደ መፈለግ ዜና እንመለስ፡ ወይን እኮ የላቸውም ወይናቸው አልቋልና ብላ ስለምን ለመነችው ከውኃ ወይን እንደሚቀዳ ዐወቀችን ወንጌላዊው ዮሐንስ ይህም ጌታ ኢየሱስ በቃና ዘገሊላ ያደረገውን ተአምር የመጀመሪያው ነው ክብሩን አሳያቸው ደቀመዛሙርቱም አመኑበት እንዳለ። ከዚያን ጊዜ በፊት እንደዚህ አላደረገምና። ዮሐ ፪+፲፩

፰ ድንግልስ ውኃውን ወይን ወደመሆን እንደሚለውጠው አላወቀችም ነገር ግን በአብ ጥላ እንደፀነሰችው በልዑል ኃይልም እንደ ወለደችው ታውቃለችና፡ስለዚህም ድንግል የምሥራቹን ከነገራት መልአክ ዘንድ አባቱ ሰማያ ዊ እንደሆነ ተረድታለችና ስለወይን ለማለደ ችው፡ስለዚህም ነገር በልቧ ድንቆችን የሚያደርግ የእርሱ ልጅ እንደ አባቱ ድንቅን ያደርጋልና አለች ደቀመዛሙርቱም አባቱን አላወቀምና ስለ ወይን ማለዱት ለእናቱም እንደነገራት መልአኩ አልነገራቸውምና የዮሴፍ ልጅ ይመስላቸው ነበር ተአምራትንም ካደረገ በኋላ ከነቢያት አንዱ እንደሆነ እንጂ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አላመኑበትም።

፴ ስለዚህም ነገር የፊልጶስ ዕፃ በምትሆን በቂሳርያ አውራጃ ሰዎች የሰውን ልጅ ማን ይሉታል አላቸው፡ደቀመዛሙርቱም ኤልያስ ነው የሚለህ አሉ ኤርምያስም ነው የሚለህ አሉ። ከቀደሙ ነቢያት አንዱ ነው የሚሉህም አሉ አሉት።እናንተስ ማን እንደሆንሁ ትላላችሁ አላቸው። ስምዖን ጴጥሮስም መልሶ አንተ የሕያው የእግዚአብሔር መሢሕ ክርስቶስ ነህ አለው የፊልጶስ ዕፃ በሆነች በቂሳርያ አውራጃ ከወልድ ሲነጋገር የጴጥሮስ ኅሊና ድንገት በመንፈስቅዱስ ክንፎች ተመሰጠ ወደ አብ አነዋወርም ደረሰ በዚያም ጌታ ኢየሱስን በአብ ቀኝ ተቀምጦ አየው ስለዚህም ወልድን አንተ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ ነህ አለው እርሱም በሰማያት ያለ አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህም ብሎ በሥጋ ኅሊና እንዳልተገለጠለት ምስክር ሆነለት።ጴጥሮስ በመንፈስቅዱስ ተመራ ከአብም ዘንድ ልቡናን ተቀበለ ከወልድም ዘንድ ኤጲስቆጶስነትን ተሾመ። አንተ አለት ነህ በአንተም ቤተክርስቲያኔን እሠራታለሁ የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈቻዎች ለአንተ እሰጥሀለሁ በምድር ያሠርኸው በሰማያት የታሠረ ይሁን በምድርም የፈታኸው በሰማያት የተፈታ ይሁን ብሎታልና። ማቴ፲፮+፲፫-፳

፲ ወበእንተዝ አእመሩ ከመ ኢተሰው አርዳኢሁ ለእግዚእ ኢየሱስ እንዘ ይትአመኑ ቦቱ ከመ ወልደ እግዚአብሔር ውእቱ አላ እንዘ የኀዝብ ልቦሙ ከመ ፩ እምነቢያት ::ወትስብእተ መለኮትሰ እምቅድስት ድንግል አኮ በሙያጤ ከመ ብእሲተ ሎጥ ዘኮነት ሐውልተ ጼው ወከመ በትረ ሙሴ ዘኮነ አርዌ ምድር እስከ ገሃየ ነቢይ እምነጽርቶ:: ሉቃ፯÷፴

፲፩ ወካዕበመ ዓዲ ኢተመይጠ ትስብእተ መለኮት ለከዊነ ኃይል ዘልማደ ሕሉና እንተ እግዚእነ::ወዓዲመ ኢተመይጠ ከመ ሙያጤ ማየ ቃና ዘገሊላ ኀበ ከዊነ ወይን:: ወእመሰ ተመይጠ ኃይለ መለኮት ለከዊነ ሰብእ እምኢተፀንሰ እንበለ ሩካቤ::ወእመሂ ተመይጠ ትስብእተ ለከዊነ መለኮት እምኢያስተርአየ ፅንሰ ድንግልና እንዘ ይልህቅ በበህቅ:: ካዕበመ እመሰ ተመይጠ መለኮት ለከዊነ ሰብእ እምኢተወልደ እምአንቀጸ ሥጋ ኅትምት:: ወእመሂ ተመይጠ ትስብእት ለከዊን መለኮት እምኢተሐቀፈ በአብራክ ወእምኢተገሰ በእደ ሰሎሜ:: ወዓዲመ እመሰ ተመይጠ ኃይለ መለኮት ለከዊነ ሰብእ እምኢያንቅዐ ሐሊበ እምአጥባተ ድንግል:: ወእመሂ ተመይጠ ትስብእት ለከዊነ መለኮት እምኢያብቀወ አፉሁ ለጠቢወ አጥባት:: ዓዲመ እመሰ ተመይጠ ኃይለ መለኮት ለከዊነ ሰብእ እምኢያስተርአዮሙ ኮከብ ዓዲመ እመሰ ተመይጠ ኃይለ መለኮት ዘትእምርተ ልደቱ ለሰብአ ሰገል እስመ ኢያስተርአየ እምቅድመ አሚሃ ኢበልደተ ቃየል ቀዳሜ ውሉድ ዘሥጋ ወኢበልደተ ሳኦል ወዳዊት ቀዳምያነ መንግሥት ዘቤተ እስራኤል:: ዓዲመ እመሰ ተመይጠ ኃይለ መለኮት ለከዊነ ሰብእ እምኢያስተርአዮሙ ለኖሎት በሥርዓተ ሕፃናት ንኡስ እንዘ ይሰክብ ውስተ ጎል:: ካዕበመ እመሰ ተመይጠ መለኮት ለከዊነ ሰብእ እምኢይቤ በእንተ ርእሱ እምቅድመ ይትወለድ አብርሃም ሀሎኩ አነ:: ወእመሂ ተመይጠ ትስብእቱ ለከዊነ መለኮት እመ ኢልህቀ በበህቅ ወእምኢወርዘወ በአምጣነ ብእሲ:: ካዕበመ እመሰ ተመይጠ ኃይለ መለኮት ለከዊነ ሰብእ እምኢረሰዮ ለማይ ወይነ በቃና ዘገሊላ:: ወእመሂ ተመይጠ ትስብእት ለከዊነ መለኮት እምኢይቤላ ለሳምራዊት አስትዩኒ ማየ::ወእምኢይቤ ካዕበ በዲበ ዕፀ መስቀል ሶበ ሰቀልዎ አይሁድ አሚሃ በውስተ መስቀል ጸማዕኩ::

፲፪ ካዕበመ እመሰ ተመይጠ ኃይለ መለኮት ኀበ ከዊነ ሰብእ እምኢጥዕመ ሞተ ወእመሂ ጥዕመ ሞተ እምንሕለ ምጽናዓተ ሰማይ ወእምተዘርዉ መሠረታተ ምድር እስመ አኃዚሁ ለዓለም ኃይለ መለኮት ውእቱ::ወእመሂ ተመይጠ ትስብእት ለከዊነ መለኮት እምኢተእ

፲ ስለዚህም ደቀመዛሙርቱ ልባቸው ከነቢያት አንዱ እንደሆነ እያሰበ እንጂ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምነው ጌታ ኢየሱስን እንዳልተከተሉት ዐወቁ::ከቅድስት ድንግል የመለኮት ሰው መሆን ግን የጨው ሐውልት እንደ ሆነች እንደ ሎጥ ሚስት ነቢይ እርሱን ከማየት የተነሣ ሁለተኛም እስኪሸሽ ድረስ እባብ እንደሆነ ሁለተኛም ጅራቱን ይዞ እስኪያነሣው ድረስ በትር ወደ መሆን እንደ ተለወጠ እንደ ሙሴ በትር በመለወጥ አይደለም:: ሉቃ፯÷፴

፲፩ ዳግመኛም ከእንደገና የመለኮት ሰውነት የጌታችን አኗኗር ልማድ ኃይል ወደ መሆን አልተለወጠም ከእንደገናም እንደ ቃና ዘገሊላ ውኃ ወይን ወደመሆን መለወጥም አልተለወጠም የመለኮት ኃይል ሰው ወደመሆን ተለውጦ ቢሆን ያለሩካቤ በተፀነሰ ነበር ሰብእና መለኮት ወደመሆን ተለውጦ ቢሆን የድንግልና ፅንስ በየጥቂቱ ሲያድግ ባልታየ::ዳግመኛም መለኮት ሰው ወደመሆን ተለውጦ ቢሆን በታተመች አፈ ማኅፀን ባልተወለደ:ሰብእናም መለኮትን ወደ መሆን ተለውጦ ቢሆን በጉልበት ባልታቀፈ በሰሎሜም እጅ ባልተዳሰሰ ከእንደገናም የመለኮት ኃይል ሰው ወደመሆን ተለውጦ ቢሆን ከድንግል ጡቶች ወተት ባልፈሰሰ ነበር: ሰብእና መለኮትን ወደመሆን ተለውጦ ቢሆን ጡት ለመጥባት አፉን ባልከፈተ ዳግመኛም መለኮት ሰው ወደመሆን ተለውጦ ቢሆን ኖሮ የመወለዱ ምልክት የሆነ ኮከብ ለሰብአ ሰገል ባልታያቸው የሥጋውያን ልጆች ፊተና ቢሆን በቃየል መወለድ የእስራኤል ቤት መንግሥት ጀማሪች በሆኑ በሳኦልና በዳዊት መወለድ ጊዜም ቢሆን ከዚያን ጊዜ አስቀድሞ አልታየምና::ሁለተኛም የመለኮት ኃይል ሰው ወደመሆን ተለውጦ ቢሆን በታናናሽ ሕፃናት ሥርዓት በበረት ተጥሎ ለእረኞች ባልታያቸው: ሁለተኛም መለኮት ሰው ወደ መሆን ተለውጦ ቢሆን ስለራሱ አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ ባላለ::ሰውነት መለኮት ወደ መሆን ተለውጦ ቢሆን በየጥቂቱ ባላደገ በሰውም መጠን ባልጐለመሰ:: ሁለተኛም የመለኮት ኃይል ሰው ወደመሆን ተለውጦ ቢሆን በቃና ዘገሊላ ውኃውን ወይን ባላደረገ ሰውነት መለኮት ወደ መሆን ተለውጦ ቢሆን ምራዊቷን ሴት ውኃ አጠጪኝ ባላላት በመስቀልም ላይ ሐሰተኛ አይሁድ በሰቀሉት ጊዜ ያን ጊዜ በመስቀል ላይ ተጠማሁ ባላለ::ማቴ፳፯÷፪ ዮሐ፳÷፴፱ ፣፲፱÷፳፰

፲፪ ዳግምኛም የመለኮት ኃይል ሰው ወደመሆን ተለውጦ ቢሆን ሞትን ባል ቀመሰ ሞትንም ቢቀምስ የሰማይ ጠፈር በፈረሰ የምድርም መሠረታት በተበታተኑ ዓለምን የያዘው የመለኮት ኃይል ነውና::ሰብእና መለኮትን ወደመሆን ተለውጦ ቢሆን ለሰቃዮች ባልተያዘ

ኀዘ ለሰቃልያን ወእምኢተዐገሠ ኀፍረተ መስቀል
እስመ መለኮትሰ ኢይትለከፍ በእእዳው ወኢ
ይትኔጸር ለዓይን ወኢይትረከብ ለኀሊና። ዓዲ
መ እመሰ ተመይጠ ኃይለ መለኮት ለከዊነ ሰብእ
እምኢይቤ ንሥት ለዝንቱ ቤተመቅደስ ወበሠ
ሉስ መዋዕል አነሥኦ።ወእመሂ ተመይጠ ትስብ
እት ለከዊነ መለኮት እምኢተወክፈ ሕማመ
ወሞተ እስመ ዘይቤ ንሥት ለዝንቱ ቤተ
መቅደስ ይቤ አነ አነሥኦ በሣልስት ዕለት።ናሁኬ.
በድን ወመንሥኢ በአሐቲ ጽምረት ድሙር
በኢብዑድ ኅቡር በኢቱሳሔ ዕቁብ በኢሙያጤ።
ውእቱመ ዘተንሥአ በተዋሕዶ ወዐርገ ውስተ
ሰማያት በ፩ ገጽ ወነበረ በየማነ እግዚአብሔር
አቡሁ በ፩ አካል ወኢይትክሀል ከመ ይትበሀል
በእንቲአሁ ንስግድ ለመለኮቱ ዘፈጠረነ ወንት
ቀነይ ለትስብእቱ ለዘዐርገ እምኀቤነ። አላ ይትበ
ሀል ንስግድ ወንትቀነይ ለኢየሱስ ክርስቶስ
ዘሎቱ ስብሐት ለዓለመ ዓለም አሜን፡ወአሜን።
ዮሐ፪÷፲፱ ሮሜ፰÷፴፬

፲፫ ተፈጸመ ዘለፋሆሙ ለእለ ይብሉ
ተመይጠ ቃለ መለኮት ኀበ ትስብእት ወትስብ
እትኒ ለከዊነ መለኮት፡ እሉ እሙንቱ መዛግብተ
ሐሰት፡ የአክዩ እምነ አጋንንት ወይረኩሱ እምነ
ከለባት፡ ይቤ ጊዮርጊስ ርቱዐ ሃይማኖት፡ ለአሉ
ሎቱ ሥርየተ ኃጢአት፡ እለ ተቀደስክሙ በደመ
ሥርዓት፡ ለዓለመ ዓለም፡ አሜን።

........ /// ............

በመስቀል ላይ እፍረትንም ባልታገሠ መለኮት
በእጅ አይነካም ለዓይንም አይታይም በኅሊናም
አይመረመርምና።ሁለተኛም የመለኮት ኃይል
ሰው ወደመሆን ተለውጦ ቢሆን ይህን ቤተ መ
ቅደስ አፍርሱት በሦስት ቀንም እነሣዋለሁ ባላ
ላቸው፡ ሰብእናም መለኮትን ወደመሆን ተለውጦ
ቢሆን ሕማምና ሞትን ባልተቀበለ ይህን ቤተ
መቅደሱ አፍርሱት ያለውን እኔ በሦስት ቀን
እነሣዋለሁ ብሏልና፡እነሆ ሟችና አስነሺው በአ
ንዲት ጥምረት ባለመለየት አንድ የሆነ ባለ መቀ
ላቀል የተባበረ ባለመለመጥ የተጠበቀ ነው
በተዋሕዶ የተነሣው እርሱ ነው። በአንድ አካል
ወደ ሰማያት ዐረገ በአባቱ በእግዚአብሔር ቀኝም
በአንድ አካል ተቀመጠ ስለርሱ ለፈጠረን ለመ
ለኮቱ እንስግድ ከእኛ ዘንድ ላረገ ለሰውነቱ እንገ
ዛለን ይባል ዘንድ አይቻልም ምስጋና ለሚገባው
ለኢየሱስ ክርስቶስ እንስገድ እንገዛም ይባላል
እንጂ ለዘላለሙ አሜን አሜን። ዮሐ ፪÷፲፱
ሮሜ፰÷፴፬

፲፫ የመለኮት ቃል ሰው ወደመሆን ሰውነትም
መለኮትን ወደመሆን ተለወጠ የሚ ሉት ሰዎች
ተግሣጽ ተፈጸመ፡ እኒሁም የሐሰት መዝገቦች
ናቸው ከአጋንንት ይልቅ ይከፋሉ ከውሾችም
ይልቅ የረከሱ ናቸው፡ለሃይማኖቱ የቀና ጊዮርጊስ
ተናገረው በሥርዓት ደም የከበራችሁ የኃጠአት
ሥርየትን ለምኑለት ለዘላለሙ አሜን።

....... /// ........

www.ethiopianorthodox.org